## የሰንደቅ ዓላማ ቀን በዋሽንግተን ዲሲ ተከበረ

የኢትዮጵያ ሰንደቅ ዓላማ ቀን አያሌ ኢትዮጵያውያንና ትውልድ ኢትዮጵያውያን በተገኙበት ለሁለተኛ ጊዜ በዋሽንግተን ዲሲ የኢትዮጵያ ኤምባሲ አዳራሽ በደማቅ ሥነ ሥርዓት ተከብሯል፡፡

በትናንትናው እለት ቅዳሜ መስከረም 30 ቀን 2002 ዓ.ም ከሰዓት በኋላ በተከበረው በዚሁ የባንዲራችን በዓል ልዩ ልዩ መልእክቶችን ያንፀባረቁ ቅስቶች በአዳራሹ ላይ የተሰቀሉ ሲሆን በበዓሉ ላይ ከሜሪላንድ፣ ቨርጂኒያ፣ ዋሽንግተን ዲሲና አካባቢዋ የተገኙት እንግዶች የኢትዮጵያን ሕዝብ መዝሙር በህብረት ዘምረዋል፡፡

በሥነ ሥርዓቱ ላይ አምባሰደሩን በመወከል አቶ ወንድሙ አሳምነው በዓሉን አስመልክቶ ባደረጉት ንግግር ባንዲራችን የመላው የኢትዮጵያ ሕዝቦች በመከባበርና በእኩልነት የመኖር ምልክት የመሆኑን ያህል በመላው ዓለም የሚገኙ ጥቁር ሕዝቦች የነፃነት ተስፋና የመስዋትነት ዓርማ ነው ካሉ በኋላ ባንዲራችን የተረጋጋች፣ የለማችና የጠነከረች ሀገር መለያ እንዲሆን የበኩላቸውን አስተዋጽኦ እንዲያደርጉ ጥሪ አቅርበዋል፡፡

በበዓሉ ስነ ሰርዓት ወቅት ባንዲራችንን የተመለከቱ ግጥሞችና ስነ ጽሁፎች የቀረቡ ሲሆን በበዓሉ ላይ የተገኙት እንግዶች የኢትዮጵያን ሰንደቅ ዓላማ በብሄራዊ መዝሙር በማጀብ የባንዲራ መስቀል ሥነ ሥርዓት አከናውነዋል፡፡